

# የቤተክርስቲያን ታሪክ

2014 ዓ.ም

# ትርጉም

- ቤተክርስቲያን ለሚለው ቃል ሦስት ዋና ዋና ትርጉሞች በሃይማኖት ትምህርት ይሰጠዋል፡፡
  - ∞ ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች ማደሪያ
  - ∞ እያንዳንዱ ክርስቲያን
  - ∞ የክርስቲያኖች ኅብረት

# 'ቤተክርስቲያን'

- **'ቤተክርስቲያን'** የሚለው ቃል በመጀመሪያ የተጠቀመበት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በቅዱስ ወንጌል እንመለከታለን። (ማቴ 16÷18፤18÷18)
- ምእመናን (ደቀመዛሙርት) ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን የተባሉት **በአንፆኪያ** ቢሆንም ቤተክርስቲያን የሚለው ስያሜ ቀድሞ በጌታችን የተሰጠን ስለሆነ አምላካዊ ስጦታችን ነውና እንጠብቀዋለን።፡

# የቤተክርስቲያን ታሪክ

## መነሻ

- የቤተክርስቲያን ታሪክ መነሻ **ዓለመ መላእክት** ነው።

- እግዚአብሔር ግዕዛን ካላቸው ፍጥረታት ጋር ያለውን ግንኙነት ቤተክርስቲያን ስለምንል መላዕክት ሲፈጠሩ በ 3 ሰማያት በ10 ከተሞች የነበረውን አገልግሎት የቤተክርስቲያን ታሪክ ጅማሬ እንለዋለን!

# ቤተክርስቲያን በብሉይ ኪዳን

- ዘመነ አበው
  - ከአዳም እስከ ሙሴ
- ዘመነ መሳፍንት
  - ከሙሴ እስከ ሳሙኤል
- ዘመነ ነገስታት
  - ከንጉስ ዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ
- ዘመነ ካህናት ወነብያት
  - ከባቢሎን ምርኮ መልስ እስከ ጌታ መምጣት

# አማናዊቷ ቤተክርስቲያን

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አንተ ጴጥሮስ ነህ ፣ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያን እሰራለሁ ፣ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም” (ማቴ 16÷18) በማለት እንደገለፀው አማናዊቷን ቤተክርስቲያን **በአለተ ዓርብ በደሙ መሠረታት!**

- አማናዊቷ ቤተክርስቲያንም ታሪክ እንዲሁ በዘመን ይከፋፈላል።

# ዘመነ ሐዋርያት ከክርስቶስ መወለድ እስከ 70 ዓ.ም

1. ቅዱስ ጴጥሮስ (ስምኦን ወይም ኬፋ)
2. ቅዱስ እንድርያስ እኁሁ ለጴጥሮስ
3. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደዘብዴዎስ
4. ቅዱስ ዮሐንስ ወልደዘብዴዎስ
5. ቅዱስ ፊልጶስ
6. ቅዱስ በርተለሜዎስ
7. ቅዱስ ቶማስ ዘህንደኬ ዲድሞስ
8. ቅዱስ ማቴዎስ (ቀራጭ የነበረው)
9. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደእልፍዮስ
10. ቅዱስ ታዲዎስ (ልብድዮስ)
11. ቅዱስ ስምዖን ቀነናዊ (ናትናኤል)
12. ቅዱስ ማትያስ - በይሁዳ ምትክ የተነሳው

# የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች

- በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቤተክርስቲያን በ120ው ቤተሰብ ደርጅታ እንደገናም ከመጀመሪያው የቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት በኋላ ማኅበረ ክርስቲያን ወደ 3ሺ ሲደርሱ በኋላም 5ሺው ተጨምረው 8ሺ ደረሱ።
- በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ውስጥ በተመሠረተችው ቅድስት ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች ወይም የአማኞች ቁጥር እየበዛ ይሄድ ነበር።
- ይኸውም በክርስቲያኖች መካከል የነበረው የእርስ በእርስ ፍቅርና መተሳሰብ በዙሪያቸው የሚኖሩ ያላመኑ አሕዛብን ያስቀናቸውና ይስባቸው ነበር። በመፈቃቀራቸውም የክርስቶስ ደቀመዛሙርት መሆናቸውን አስመስክረዋል!
- **የአጋፔ ኑሮ**

# . . የቀጠለ

- ቤተክርስቲያን በዚህ ዘመን ወደ አሕዛብም ምድር መስፋፋት በመጀመሯ በርካታ አህዛብ ወደ ክርስቶስ ትምህርት ቀረቡ ክርስቲያኖች ሆኑ!

- ቤተክርስቲያን በቤተ-አይሁድ እና በቤተ-አሕዛብ የተለያየ መልክ ነበራት።

# . . በቤተ አይሁድ

- ቀድሞውንም ስብከተ ነቢያትን በመስማት መሲሁን ሲጠብቅ የነበረ ህዝብ
- የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያኖች
- የመጀመሪያዎቹን መጻህፍት እና የጸሎት ስፍራዎችን

# . . በቤተ አሕዛብ

- በብዙ አማልክት ማመን የነበረ ህዝብ
- የሥነ ምግባር ችግሮች የነበሩበት በተለይ ሴቶች እና ባሪያ ተብለው በሚኖሩ ሰዎች ላይ
- ከጣኦት አምልኮ በተጨማሪ በበርካታ የፍልስፍና ትምህርቶች ግራ የተጋቡ ነበሩ
- በቶሎ የሚሰበር ልብ እና በፍጥነት ወደ ክርስቶስ ማመን የመጡ ህዝቦች

# የዘመኑ ዓበይት ክስተቶች

- ማህበረ ቅዱስ እስጢፋኖስ
- ሰማዕትነት መጀመሩ
- የቅዱስ ጳውሎስ መጠራት
- የመጀመሪያው የኢየሩሳሌም ጉባዔ
- የኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም በጥጦስ መጥፋት

# ..የቀጠለ

- ከኢየሩሳሌም መጥፋት በኋላ ሌሎች የክርስቲያኖች መንበሮች እየተጠናከሩ መጡ። ለምሳሌ

## የአንጾኪያ መንበር

- አንጾኪያ ለሮም አስተዳደር ሶስተኛ ከተማ የነበረች የሶርያ ከተማ ነች፡፡ በዚህች ቦታ ቀድመው ወንጌልን የሰበኩት ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ ሲሆኑ ቅዱስ ጴጥሮስም ሰብኮባታል፡፡ በከተማዋ አይሁድም አህዛብም ነበሩባት፡፡

- የጌታ ደቀመዛሙርት ክርስቲያን የሚለውን ስም ያገኙት በዚህች ከተማ ነው፡፡

# ..የቀጠለ

## የእስክንድርያ መንበር

- የእስክንድርያ ከተማ በግብጽ ሰሜናዊ ጫፍ በአባይ ወንዝ ዳርቻ የምትገኝ ወደብ ናት፡፡ ከተማዋ ስሟን ያገኘችው ከታላቁ የመቄዶንያ ተወላጅና የግሪኮች ንጉስ ከነበረው ከእስክንድር ነው፡፡

- መንበሩን የመሰረተው ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ በ፶ ዓ.ም ነው በ፷፰ ዓ.ም በሰማዕትነት ሲያርፍ ቅዱስ አንያኖስ በመንበሩ ተተክቶአል፡፡ ዛሬ የግብጽ ቤተክርስቲያን ዋና ማዕከል ናት፡፡

# ..የቀጠለ

## የሮማ መንበር

- የሮም መንግስት ዋና ከተማ ናት፡፡ በዚህችም ከተማ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን በስፋት እንደሰበከና የመጀመሪያዎቹ ጳጳሳት ቅዱስ ሌናስንና ቅዱስ አኔቅሊጠስን እንደሾማቸው ይነግረናል፡፡

- የሮም ሰዎች በሮም ከተማ በመጀመሪያ የሰበከው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

## ..የቀጠለ

# የቁስጥንጥንያ መንበር

- የቁስጥንጥንያ ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ የተሰበከችው በሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ነው፡፡ ከተማዋ የምሥራቃዊ ሮም ግዛት (የቢዛንታይን) መናገሻ ነበረች፡፡
- ይህች መንበር እና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የመሰሉ ታላላቅ የተዋህዶ ሊቃውንት ያፈራች ናት፡፡

# ዘመነ ሐዋርያን አበው

## ከ70 ዓ.ም - 160ዓ.ም

- በዚህ ዘመን ለቤተክርስቲያን ጠበቆች የሆኑ በአፍ በማስተምር በተለይ ደግሞ በጽሁፍ ቤተክርስቲያንን በሚመለከት መልስ የሚሰጡ አባቶች የተነሱበት ነው።

ለአብነትም ፡

- ቅዱስ ቀለሜንጦስ
- ቅዱስ ፖሊካርፐስ
- ቅዱስ ሔሬኒዮስ
- ጠርጥሉስ ፣ አቴና ጎራስ ፣ሰማዕቱ ዮስጦስ

የመሳሰሉትን ማንሳት እንችላለን!

# ዘመነ ሰማእታት ከ160 ዓ.ም እስከ 312 ዓ.ም

- ቤተክርስቲያን ተጋድሎ በዘመነ ሐዋርያት በአብዛኛው በአይሁድ የመጣ ፈተና ነበር፡፡ አይሁድ ክርስትና እንዳይስፋፋ ለማድረግ ሐዋርያትን ማሳደድ ቢጀምሩም ማህበረ እስጢፋኖስን ቢበትኑም ክርስትና እንዳይስፋፋ ለማድረግ ከቶውንም አልቻሉም፡፡
- ይልቁንም አይሁድ መጽሀፍትና ሕግ ያላቸው የነቢያትም ትንቢት የሚያውቁ ስለሆነ ከእነርሱ ጋር የሚደረገው ውይይት ክርክር ቀለል ያለ ነበር፡፡ ሐዋርያትም የመጽሐፍ ክፍል እየጠቀሱ ለማብራራት አልተቸገሩም ነበር፡፡
- ክርስትናን በአህዛብ ምድር ሲሰበክ ግን በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ መከራ ደርሶባታል፡፡ አህዛብ ሕግ ያልነበራቸውና የሚመራቸው መጽሐፍ ስላልነበራቸው የደረሰባቸው ፈተና ከበፊቱ እጅግ የበዛና ከባድም ነበር፡፡ ቤተክርስቲያን ከአህዛብ ጋር ያደረገችውን ትግልና በአላውያን ነገስታት እና በጣዖት ካህናት በርካታ መከራ ደርሶባታል።

# በኔሮን ቄሳር ዘመነ መንግስት ከ57-68ዓ.ም

- ኔሮን አሮጌውን ከተማ አዲስ ከተማና ሰፊ ቤተመንግስት እንዲሰራ በማሰብ በ57 ዓ/ም የሮምን ከተማ 2/3ኛውን በእሳት አቃጥሏል፡፡
- በዚህም የተነሳ በሀብቱ መቃጠልና በዘመዶቹ መሞት ከተቆጣው ህዝብ ለማምለጥ በሀሰት ይህን ቃጠሎ ያስነሱት ክርስቲያኖች ናቸው በማለት ክርስቲያኖች ላይ አመካኝቶባቸዋል፡፡
- ክርስቲያኖች ላይም ብዙ ስቃይና ሞት አድርሶባቸዋል፡፡ በዚህ ዘመን ቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስም ብዙ ተጋድሎ ፈጽመው በሰማእትነት አርፈዋል፡፡

# በድምጥኖስ ዘመነ መንግስት ከ81-96ዓ.ም

- ድምጥያኖስ ከኔሮን ቀጥሎ በክርስቲያኖች ላይ ብዙ መከራና ስቃይ በማድረስ የታወቀ ነው። ድምጥያኖስ የራሱን ምስል አሰርቶ እንዲሰግዱለት ወደ ኤፌሶን ልኮት ነበር።
- ያን ጊዜ በኤፌሶን የነበረው ወንጌላዊው ዮሐንስ እና በኤፌሶን የነበሩ ክርስቲያኖች ተቃውመውት ነበር።
- በዚህም የተነሳ ዮሐንስ ለእስራትና ለእንግልት ክርስቲያኖችንም ለመከራ እንዲዳረጉ አድርጓቸዋል!

# ▷ በትራጀን ዘመነ መንግስት

**ከ98-117ዓ.ም**

- በትራጀን ዘመነ መንግስት ክርስቲያኖችን በኃይል ብቻ ሳይሆን በዘዴና በማስፈራራትም ጭምር ወደ ቤተ ጣኦት ለመመለስ ይሞክር ነበር።

- በዚህ ዘመን ቅዱስ አግናጥዮስ ሰማእትነቱን ተጋድሎ ፈጽሟል። በቲያትር ማሳያ ቦታ ለነበሩ አናብስት ተጥሏል ለዚህም ነው **ምጥው ለአንበሳ** የሚል ስም ያገኘው!

# ▷ በዳክዮስ ዘመነ መንግስት ከ249-251 ዓ.ም

∞ በየዘመኑ ከነበሩ ቄሳሮች ከበድ ያለ አዋጅ በማሳወጅ ክርስቲያኖች መከራ የገጠማቸው በዳክዮስ ዘመን ነበር፡፡ ዳክዮስ የክርስቲኖችን መመሪያ አጥንቶ ከአማካሪዎቹ ጋር ተመካክሮ የሚከተለውን አዋጅ አውጇል፡፡

∞ አዋጁም ‹‹በሮም ግዛት በሮማዊ ዜግነት የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በሮም ባህል መሰረት የሮማ መንግስት ሕጋዊ ነው ብሎ የተቀበለውንና ነገስታቱም ሲያመልኳቸው የነበሩ ጣኦታትን በግዴታ እንዲያመልኩና መባዕ እንዲያቀርቡ የሚል ነበር፡፡

∞ ይህን ያልፈጸመ ሁሉ በሞት እንዲቀጣ የሚል ነበር›› ክርስቲያኖቹም ለዚህ አዋጅ ተገዢ ስላልነበሩ ህይወታቸው በሰማዕትነት እንዲያልፍ ሆኗል፡፡ ከዚህ ዘመን ጀምሮም ክርስቲያኖች ከስቃይ ለማምለጥና ሃይማኖታዊ ተልእኳቸውን ለመፈጸም እንዲችሉ በተለይም በሮምና በአካባቢዋ ዐለት በመፈለግ በአካባቢው ዋሻ በማዘጋጀት ወደ ግበበ ምድር የገቡት፡፡

# ▷በዲዮቅልጢያኖስ ዘመነ መንግስት

## ከ284-305 ዓ.ም

- ከላይ ከተገለጹት ቄሳሮች በኋላ በአይነቱም ሆነ በግፉ ተወዳዳሪ የሌለው የክርስቲያኖች እልቂት የተፈጸመው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ነበር፡፡ ዲቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን አጥብቆ እንዲጠላ ያደረጉት ሁለት ነገሮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

- ጋሌርዮስ የተባለ የልጁ ባል (አማቹ) ክርስቲያኖች አጥብቆ ስለሚጠላ በእርሱ ምክር በመመረዝ እና እንደ ሌሎቹ ቄሳሮች የራሱን ምስል አሠርቶ ስገዱልኝ በማለቱ ክርስቲያኖች ደግሞ አንሰግድም በማለታቸው ነው፡፡

# . . በዲዮቅልጢያኖስ የወጡ አዋጆች

- አብያተ ክርስቲያናት እንዲደመሰሱ
- ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው እንዳይገናኙ
- ስለክርስትና ሃይማኖት የሚናገሩ መጽሐፍት በጠቅላላ እንዲቃጠሉ
- የቤተክርስቲያን ንብረት የሆነ ሁሉ እንዲወረስ
- ማንኛውም የሮማ ዜጋ ክርስቲያን ከሆነ ከመንግስት ሥራው እንዲወገድ
- ባሮች ክርስትናን ከተቀበሉ ነፃ የመውጣት መብት እንዳይኖራቸው
- ክርስቲያኖች ምንም ህጋዊ ምክንያት ቢኖራቸው በማንም ላይ ክስ መመስረትና ስለ መብታቸው መከራከር አይችሉም የሚል ነበር፡፡

ስ ብ ሐ ት

# ለእግዚአብሔር

## ዘመነ አበው ከ 325- 451

ከጉባዔ ኒቂያ እስከ ኬልቄዶን